# በ2007 ለሚካሄደው ለአምስተኛ ዙር ብሔራዊ ምርጫ የተዘጋጀ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት

## መድረክ /መድረክ/ ማኒፌስቶ፡-

### መግቢያ፡-

በአሁኑ ወቅት የዓለማችን ሕብረተሰብ የግለሰብና የቡድን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረውለት፣ ሀሳቡን በነጻነት እየገለጸና መረጃዎችን እየተለዋወጠ፣የመረጠውን የፖለቲካ አመለካከት እያራመደና በፈለገበት የፖለቲካ ድርጅት እየተደራጀ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫና ነጻና ገለልተኛ ዳኝነት በተግባር ተረጋግጠውለት የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ለማድረግ እያካሄደ ያለው ትግል በብዙ አከባቢዎች ውጤታማ እየሆነ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችንና ሕዝቦቹዋ ግን ከብዙ ጊዜያት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የአምባገነን መንግሥታት መፈራረቂያ እንደሆኑ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት ሀገራችንን እየገዛት የሚገኘው ገዥ ፓርትም (ኢህአዴግም) ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እየገነባሁ ነኝ እያለ ብዙ ቢደሰኩርም ባለፉት 23 ዓመታት በተግባር ያሳየን እውኔታ የራሱን የጨቋኝ አገዛዝ የማስቀጠል ምኞት አራማጅነቱን ብቻ ነው፡፡ ይኼው ገዥ ፓርቲ የአምባገነንነት አገዛዝ ፍላጎቱን በፕሮፓጋንዳ ጋጋታ እየሸፋፈነ በተግባር ግን የሀገርቱን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቅላይነቱን በኃይል እያረጋገጠ የሕዝባችንን የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ ተስፋ እያጨለመው ይገኛል፡፡ ለፖለቲካ ፍጆታ ብሎ ያወጣቸው ሕገ-መንግሥትም ሆነ የተለያዩ ሕጎች በወረቀት ላይ ብቻ እንዲቀሩና ተግባር ላይ እንዳይውሉ በማድረጉ ዛሬ ሀገራችን የሕግ የበላይነት ሳይሆን የገዥው ፓርቲ መሪዎች የበላይነት ብቻ የተረጋገጠባት ሆናለች፡፡ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት ሕዝባችን በአምባገነናዊ አገዛዝ ሥር ወድቆ ይገኛል፡፡ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹ በታፈኑበትና ፍትሕ፣እኩልነትና መልካም አስተዳደር በሌሉበት ሥርዓት ለመኖርም ተገዷል፡፡

ኢህአዴግ የመንግሥት ሥልጣንን ያለአግባብ እየተጠቀመ የመንግሥትንና የሕዝብን ሀብትና ንብረት ለአምባገነናዊ ሥርዓቱ ማጠናከሪያ የሆነውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ በግድ ለማሰረጽ እየተገለገለበት ነው፡፡ የራሱን ፓርቲ ሥራዎች በሙሉ በማንአለብኝነት በመንግሥት ሀብትና ንብረት እየተጠቀመ በመሥራት ላይ ያለው ኢህአዴግ ተወዳዳሪዎች ሳይሆኑ አጎብዳጆቹና አጃቢዎቹ ብቻ ሆነውና ለማስመሰያ ዴሞክራሲው መሸፈኛ ሆነው እንዲያገለግሉት ለመረጣቸው አንዳአንድ ተቃዋሚ ነን ለሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የተለያዩ መደለያዎችን ከሕግ ውጭ ከመንግስት ገንዘብ እንዲያገኙና ፀረ-ዴሞክራሲያዊና ሕገ-ወጥ አካሄዶቹን እንዲሸፋፍኑለት በማድረግ ላይ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከእርሱ የተለየ አማራጭ ፖሊሲ በነፃነት የሚያራሚዱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ግን ከመንግሥት ምንም አይነት ድጋፍ እንዳያገኙ ከማገዱም በላይ እነዚሁ ተቃዋሚ

ፓርቲዎች ከአባሎቻቸው መዋጮና ከደጋፍዎቻቸው በሚያገኙት አነስተኛ ገንዘብ በየአከባቢው የተለያዩ ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎችንና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን እንዳያካሄዱ ገደብ የለሽ ጫናዎችን በመፈጸም ላይ ይገኛል። በዚሁም መሠረት አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን ለእስራት፣ለስደት፣ለስራ አጥነትና ለመሳሰሉት እንግልቶች እየዳረገና ግዲያም እየፈጸመባቸው ፓርቲዎቹን የማዳከምና የማቀጨጭ ዘመቻውን አጠናክሮ በማካሄድ ላይ ይገኛል። ሕዝባችን አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በነፃነት እንዳይመርጥ የምርጫ አስተዳደሩ በአባላቱና ደጋፊዎቹ እንዲሞላና በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር እንዲሆን ስላደረገው ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደር በሀገራችን ሊኖር አልቻለም። በዚሁም ምክንያት ምርጫውን የሚያስተዳድረው ተቋም ኢህአዴግ ከሕግ ውጭ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ሁሉ በቸልታ የሚመለከትና የሚሸፋፍንለት በመሆኑ የሕዝባችን የሥልጣን ባለቤትነት ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም።

የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከደርግ የአንድ ርዕዮትና የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አላቅቃለሁ በማለት የሸንገላ ፕሮፓጋንዳውን ሲያሰራጭ የነበረው ኢህአዴግ ልክ እንደ ደርግ (ከማስመሰያ ሽፋኑ በስተቀር) በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር እየተመራ ሌሎች አማራጭ አስተሳሰቦችን በጠላትነት እየፈረጀ በመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ፋንታ በዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሕ ዴሞክራሲን ሸብቦ የራሱን ፈለጭ ቆራጭ አገዛዝ አስፍኖ ይገኛል። በመሆኑም በሃገራችን ዛሬም እንደቀድሞው የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እየተረገጡ ናቸው። የሕግ የበላይነትና ነፃና ገለልተኛ የፍትሕ ሥርዓት የለም። ነፃና ፍትሐዊ ምርጫና ነፃው ፕረስም ደብዛቸው እየጠፋ ነው። ከኢህአዴግ የተለየ አማራጭ የሚከተል ነፃ የፖለቲካ ፓርቲን አደራጅቶ መታገል ለከፋ እንግልት የሚዳርግ ተግባር ሆኖአል።

ለዘመናት ሳይፈታ የኖረው የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ዛሬም መፍትሄ ሳያገኝ በመቅረቱ ሀገራችንን የባሰ ውስብስብ ችግር ውስጥ እንዳይከታት የሚያሳስብበት ደረጃ ላይ ደርሶአል። በአሁኑ ወቅት በብዙ የሀገራችን ክልሎች አዋሳኝ አከባቢዎች በሚኖሩ ሕዝቦቻችን መካከል ግጭቶች እየተከሰቱ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል። የዜጎች በፈለጉበት አከባቢ ሠርቶ የመኖርና የልማት ተግባር የማከናወን መብት አለመከበርና የስራ ዋስትና አለመኖር በሕዝቦች መካከል ሊኖር የሚገባውን መቀራረብ እያደፈረሰውና የሕዝቡንም የሀገሩ ባለቤትነት መንፈስ እያዳከመው በመሄዱ እነዚህ ሁኔታዎች በአጠቃላይ የኢህአዴግ መንግሥት ሀገራችንን አስጊ ሁኔታ ውስጥ እየከተታት መሆኑን አመላካቾች ሆነው ይገኛሉ። ጦረኛና ሽብርተኛ ብሎ ከፈረጃቸው ድርጅቶች ጋር እየተወያየ ያለው ኢህአዴግ እነዚህን የሀገራችንን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር ለመፍታት እንዲቻል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት በተደጋጋሚ ላቀረባቸው የሰላማዊ ውይይትና ድርድር ጥያቄዎች የእምብተኝነት ምላሽ በመስጠትም በአፍራሽ ተግባሩ ቀጥሎበታል።

የኢህአዴግ የተሳሳቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ያስገኙት ድምር ውጤትም ረሃብና ችጋር፣ አስከፊ የኑሮ ውድነት፣ድህነት፣ስደትና ሥራ አጥነት በአጠቃላይም ያፈጠጠ የጥቂቶች መበልጸግና የብዙሀኑ መጎሳቆል ሆኖ ይገኛል። ይህ ሁኔታ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ላይ እየደረሰ ቢሆንም በተለይ በወጣቱ ላይ በአስከፊ ሁኔታ እየተንጸባረቀ በመሆኑ የሀገራችን

*ተተኪ ትውልድ ለከፍተኛ ተስፋ መቁረጥና ስደት እየተዳረገ ይገኛል። ኢህአዴግ የሀገራችንና የሕዝባችንን ችግሮች በተጨባጭ እየፈታ ዓለም ወደ ደረሰበት ዘመናዊ ሕብረተሰብ ግንባታ ከመጓዝ ፋንታ ከወደቀው የደርግ ሥርዓት ጋር እራሱን እያነጻጸረ ድክመቶቹንም በዚሁ ለመሸፋፈን እየሞከረ ይገኛል። በዚህም ኢህአዴግ ወደ ፊት ማየት በተቸገረበት አካሄዱ የሀገራችንን ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን ከመፍታት ፋንታ በተጨባጭ የሕዝባችንን ኑሮ ሲያሻሽል ያልታየውን የፈጣን ኢኮኖሚ እድገት ዲስኩር በማስተጋባት ተግባር ተጠምዶ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በአንድ በኩል ኢህአዴግ የሚያስተጋባው የሁለት አሀዝ አመታዊ እድገት ዲስኩር በሌላ በኩል ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመሄድ ላይ ያለው የሕዝባችን ድህነት፣ ሥራ አጥነትና ስደት በተቀራኒ ተፋጠው ይገኛሉ።*

*የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ሀገራችን ለብዙ ዘመናት የቆየችባቸውንና የኢህአዴግ መንግስትም የጫነበትን ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮችን ከመሠረቱ ለመፍታት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን በፖለቲካ ፕሮገራሙ ይፋ አድረጎ የቆየ ሲሆን ዋና ዋና የአማራጭ ፖሊሲዎቹን ሀሳቦች በሀገራችን በ*2007 *ለሚካሄደው የአምስተኛ ሀገር አቀፍ ምርጫ ባዘጋጀው በዚህ ማኒፌስቶው እንደሚከተለው አቅርቧል።*

## ክፍል1- *መሠረታዊ የፖለቲካ ዓላማዎችና አቋሞች፡-*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ የየራሳቸው ማንነትና መገለጫዎች ያላቸው የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንደዚሁም የተለያዩ ሀይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች በጋራ የሚኖሩባት ሕብረ-ብሔራዊት ሀገር ነች። ይህች የብዙህነት መገለጫ የሆነችው ሀገራችን ግን የዜጎችዋ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይከበሩ የብዙሀኖች መሰቃያና በየጊዜው የሚፈራረቁባት የጥቂት ፈላጭ ቆራጭ ገዥዎች መንደላቀቂያ ሆና ኖራለች። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የኢህአዴግን አምባገነናዊ ሥርዓት በማስወገድ ሀገራችን ወደ ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲትሸጋገርና ሕዝባችንም በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነትን ገንብቶ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተረጋግጠውለት የሀገራችን ሉአላዊ ሥልጣን ባለቤት እንዲሆን ለመድረግ ይታገላል። በዚሁም መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ መድረክን መርጦ ለሥልጣን ካበቃው በፖለቲካው ረገድ የሚከተሉትን አበይት ተግባራት ያከናውናል።*

1-1-*በአሁኑ ወቅት በሕዝባችን ላይ ተጭነው የሚገኙትን የኢህአዴግ አምባገነናዊ ተጽኖና አፈናዎችን በመስወገድ ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች የየራሳቸውን ፖለቲካዊ አመለካከትና ርዕዮተ-ዓለም በነፃነት የማራመድ መብታቸው የሚከበርበት የሰለጠነ ፖለቲካ ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ እንዲሰፍን ይደረጋል። ለዚህም ተግባራዊነት በተወዳዳሪ ፓርቲዎች ስምምነት ከላይ እስከ ታች ድረስ የሚቋቋም ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደርና ገለልተኛ የሀገር ውስጥ ሲቪክ ማህበራትና የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች በስፋት የሚሳተፉበት የምርጫ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል።*

1-2- በመሠረታዊ የሀገራችን ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ለሀገራችን እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ለዚህ ዓላማ ተግባራዊነት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። መድረክ በምርጫ እንዳሸነፈም ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሚያሳትፍ ብሔራዊ ፌደራላዊ አንድነት መንግሥት ያቋቁማል።

1-3- የሀገራችን ፖለቲካ ከቂም በቀልና ከጥላቻ ስሜት እንዲሁም ከተለያዩ ቁርሾዎች የሚላቀቅበት ሁኔታ እንዲፈጠርና ዜጎች የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም የአንድ መንግሥት ተቋም ባልደረባ በመሆናቸው ብቻ የማይወነጀሉበት ስርዓት እንዲፈጠር ይደረጋል።

1-4- ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲጎለብትና ሕገመንግሥቱም ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎችንና ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ ውይይት ተደርጎበት በሕዝብ ውሳኔ ጭምር የሚሻሻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ይደርጋል።

1-5- በሀገራችን የገዥዎች የበላይነት ቀርቶ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ለማድረግ እንዲቻልም በሕግ አውጭው የሚወጡት ሕጎች በሕገ መንግስቱ መሰረት መሆናቸው የሚረጋገጥበት አሰራር ይዘረጋል። የሕግ ተርጓሚ (የዳኝነት) አካሉ ከሕግ አስፈጻሚው አካል ተጽኖ ይላቀቅ ዘንድ የዳኞች ምልመላ፣ አስተዳደርና ዕድገት ከፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዳ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል። የአቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትም ከአስፈጻሚ አካላት ነፃ ሆኖ እንዲደራጅና ተልእኮውም ሕግን ማስከበር እንጂ የመንግሥትን ወይም የገዥ ፓርቲን ፖለቲካዊ ፍላጎት ተከትሎ መሄድ እንዳይሆን ይደረጋል።

1-6- በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የፓርቲና የመንግስት ሥራዎች በአግባቡ ተለይተው አለመሠራታቸው የዳኝነት ሥርዓቱ ነፃነት መገፈፍን ጨምሮ በጠቅላላ ሕገመንግሥቱ የደነገገውን የመንግስት አካላት የሥልጣን ክፍፍል ተግባራዊ እንዳይሆን ጠንቅ ሆኖ ስለሚገኝ የፓርቲ ሥራና መዋቅር ከመንግሥት ሥራና መዋቅር በትክክል መለየቱ እየተረጋገጠ የሚሠራበት ሁኔታ ይመቻቻል።

1-7- መድረክ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነትና በመከባበር ላይ በተመሠረተ ግንኙነት የሀገራችንን አንድነትና ዕድገት ለማረጋገጥና የጋራ ጥቅሞቻቸውንና እሴቶቻቸውን በጋራ ለመጠበቅ ኃይላቸውንና አቅማቸውን ማስተባበር እንደሚገባቸው ያምናል። ለዚህ ዓላማ መሳካትም በጽናት ይታገላል። በቀድሞ የነበሩትና በአሁንም ኢህአዴግ በሰፊው እያከሄደ ያለውን ብሔር ብሔረሰብን መሠረት ያደረገ መድልኦን ያስወግዳል። ሁሉም ዜጎቹዋና ሕዝቦቹዋ በእኩልነትና በመከባበር የጋራ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጡበት የሀገራችን አንድነት እንዲጠናከር አበክሮ ይሠራል። መድረክ የመገንጠልን ዓላማ የማይደግፍ ሲሆን የሀገራችን ዳር ድንበር፣ነፃነት፣ሉአላዊነትና አንድነት ተከብሮ እንዲኖር ይታገላል።

1-8- ሀገራችን የሚትከተለው የመንግሥት አወቃቀር በፌደራልና በክልል መንግሥታት የተመሠረተ ፌደራላዊ አወቃቀር ሆኖ በፌደራል መንግሥትና በክልል መንግሥታት መካከል የሚኖረው የሥልጣን ክፍፍል እና ግንኙነት ከኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርሕ ተላቅቆ አንዱ በሌላው ሥልጣን ጣልቃ ሳይገባ ሁለቱም በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው

የሥልጣን ክፍፍል የሚሠሩበት ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ የፌደራልዝም መርሕ የተከተለና በትክክልም ሥራ ላይ የሚውል እንዲሆን ይደረጋል። በሁሉም ክልሎች ሕዝቦች መካከል በእኩልነትና በመግባባት ላይ የተመሠረተ መልካም የትብብር ግንኙነቶች እንዲዳበሩ ለማድረግ መድረክ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል። ሕዝቡን በሚከፋፍሉና በሚያጋጩ ባለሥልጣናትም ሆነ ሌሎች ፖለቲከኞች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ይደረጋል። በሕብረተሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሰላማዊና ባሕላዊ ውይይቶችና እርቅ የሚወገዱበት አሰራርም ይዘረጋል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከሀገራችን ክልሎች በመረጠበት ክልል የመኖርና የሚፈለግበትን ሕጋዊ ግዴታዎችን አሟልቶ የመሥራት መብቱ በኢህአዴግ ስርዓት በትክክል ተከብሮ ሥራ ላይ ሊውል አልቻለም። መድረክ ይህ የዜጎች መብት ሳይደፈርና ሳይሸራረፍ በትክክል ተከብሮ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል። የፌደራልና የክልል መንግሥታትም ይህንኑ የዜጎች መብት የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ይኖርባቸዋል።

1-9- የፌደራል መንግሥት የሕግ አውጭ አካል ባለሁለት ምክር ቤት (Bi-cameral) ሆኖ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የሕግ መወሰኛ (የፌዴሬሽን ምክር ቤት) የሚባሉ አካላት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለቱም ምክር ቤቶች በሕዝቡ ቀጥተኛና ነፃ ተሳትፎና በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በተመረጡ የህዝብ ተወካዮች እንዲቋቋሙ ይደረጋሉ። የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወጡ ሕጎች ሕግ ሆነው ከመውጣታቸው በፊት በሕገመንግሥቱ መሠረት የወጡ መሆናቸውን መርምሮ የማጽደቅ ሥልጣንና ኃላፍነት እንዲኖረው ይደረጋል። ሕገ መንግሥት የመተርጎም ሥራ ከፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ሥልጣን ይወጣል። በምትኩም ይህንኑ ሥራ የሚሠራ ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ይቋቋማል።

1-10- በሁሉም ደረጃ ያሉ ምክር ቤቶችና አስፈጻሚ አካላት የሥልጣን ምንጭ ነጻና ፍትሐዊ የሕዝብ ምርጫ ብቻ ይሆናል። በአስፈጻሚ አካላት በፖለቲካ ሹመት የሚመደቡት ኃላፍነቶችም በሕግ የተወሰኑና ተለይተው የሚታወቁ ይሆናሉ። ከዚህ ውጭ ያሉት ኃላፊነቶችና የሥራ መደቦች በሙያ ብቃትና በአገልግሎት ላይ ተመሥርተው ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ሁሉም ዜጎች ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ ውድድር የሚመደቡበት ይሆናሉ። በዚህ መልኩም በአሁኑ ወቅት በሲቪል ሰርቪሱ ሰፍኖ ያለው የፓርቲና የመንግስት መደበላለቅ እንዲስተካከል ይደረጋል።

1-11- የሀገራችን ፖለቲካዊ ሥርዓት ፓርላሜንታዊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ፓርቲ በተከታታይ አሸንፎ ሥልጣን የሚይዝበት ሁኔታ ቢፈጠር ጠቅላይ ሚኒስተሩ ከሁለት የፓርላማ ዘመን በላይ እንዲመራ የማይፈቀድ ይሆናል።

1-12- የሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ የፖሊስ ኃይል፣ የብሔራዊ ደህንነትና ኢሚግሬሽን ባለሥልጣን ሰራተኞች፣ ዳኞችና አቃቤ ሕግ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ተግባራቸውን የሚያከናውኑ ይሆናሉ። መንግሥት በተቀያየረ ቁጥር የማይቀያየሩና እንደተቋምም ቋሚ ሆነው ለመቀጠል እንዲችሉ ከማንም ፓርቲ ጋር ሳይወግኑ ለሀገርና ለሕዝብ ሰላምና ደህንነት አገልጋዮች ብቻ ሆነው ይሠራሉ። የሀገር መከላከያና የፖሊስ ኃይል አባላትና የብሔራዊ ደህንነትና መረጃ ሠራተኞች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች

ሚዛናዊ ተዋፅኦን የጠበቀ የሰው ኃይልም እንዲኖራቸው ይደረጋል። በተላይም በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን በሕወሓት አባላት ፍጹማዊ የበላይነትና ፈላጭ ቆራቀጭነት ሥር እንዲውል የተደረገው የሀገር መከላከያ ኃይል ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አመራር ድረስ ያለው መዋቅር የሀገራችንን ሕዝቦች ትክክለኛ ገጽታ በሚያሳይ ሁኔታ ይደራጃል።

1-13- የግለሰብና የቡድን (የብሔር፣ብሔረሰቦች፣የሐይማኖቶች፣የተለያዩ ማሕበራትና ማሕበረሰቦች) መብቶች በእኩልነት እንዲከበሩና ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። ሀገራችን የተቀበለቻቸው የግለሰብና የብሔር ብሔረሰብ አለም አቀፋዊ ሰብአዊና የሲቪል መብቶች የተከበሩ ይሆናሉ።

1-14- የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ማንነታቸው የታወቀና እኩልነታቸው የተከበረ ሆኖ እያንደንዱ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ ቋንቋውን፣ ባሕሉንና ታሪኩን የመጠበቅ፣ የመጠቀምና የማዳበር እንዲሁም የማስተዋወቅ መብት ይኖረዋል። ከአማረኛ በተጨማሪ በበርካታ የሀገራችን ሕዝቦች የሚነገር ሌላ ቋንቋ (አፋን ኦሮሞ) የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ይደረጋል። ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በየአከባቢያቸው መንግሥታዊ አካላትን በማዋቀር በክልልም ሆነ በየደረጃው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኩታገጠም አሰፋፈር ያላቸው ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በስምምነት የጋራቸው የሆኑ የክልላዊ መንግሥታትና ሌሎች በየደረጃው የሚያስፈልጉ መንግሥታዊ አካላትና መዋቅሮችን በማቋቋም በጋራ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውም የተከበረ ይሆናል። በዚህ መሠረት የሚቋቋሙ የክልላዊም ሆኑ በየደረጃው ያሉ የጋራ የመንግስት አካላት በአንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ስም በየደረጃው ከሚያቋቁሙት መንግሥታዊ አካላት ጋር እኩል መብት ይኖራቸዋል። በቁጥር ብዙሃን በሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች መካከል የሚኖሩ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ሕልውናና ሁለንተናዊ መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል። በዚሁም መሠረት በአከባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርና በየደረጃው ባሉት የበላይ አካላት የመወከል መብታቸው የተከበረ ይሆናል። በአንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ መካከል የሚኖሩ የሌላ ብሔር ብሔረሰብ ተወላጆች በሚኖሩበት አከባቢ መምረጥንና መመረጥን ጨምሮ ሁሉም የዜግነት መብታቸው የተከበረ ይሆናል። ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገራችን በሚካሄደው ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። ኢህአዴግና የቀደሙት መንግሥታት በዕድገት ወደ ኋላ የቀሩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ለቱርስት መስህብነት ብቻ ሲጠቀሙ የቆዩበት ሁኔታ ተወግዶ ለእነዚህ ወገኖቻችን ልማትና የትምህርት ዕድል ማግኘት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

1-15- ማነኛውም ዜጋ የፈለገውን ሐይማኖት የመከተል መብቱ የተጠበቀ ነው። በእምነቱ ምክንያት የሚነፈገው መብትና ጥቅም አይኖርም። መንግሥትና ሐይማኖት የተለያዩ ናቸው። ስለሆነም መንግሥታዊ ሐይማኖት አይኖርም። መንግሥት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ ሀይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። በዚሁም መሠረት በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ መንግሥት ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎችን በመጣስ በሀይማኖት ተቋማት ላይ እያደረገ ያለውን ተጽኖዎች የሚያስወግዱ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። የመንግሥትንና የሀይማኖትን ሥራዎች በማደበላለቅ የሀይማኖት መሪዎች በተለይም የሙስሊሙ ሕብረተሰብ

መሪዎች ምርጫ በመንግሥት ተቋም (በቀበሌዎች) ቁጥጥር ሥር እንዲካሄድ ያደረገበትና በእምነቱ ተከታዮች ነፃ ምርጫ ተመርጠው በነፃነት እንዳይሠሩ እያደረገ ያለው ሕገ ወጥ አሰራርና ተጽኖ በአስቸኳይ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ሐይማኖቶች በመንግሥት ፊት እኩል ናቸው፡፡ መንግሥት ሁሉንም በእኩል ያስተናግዳል፣ እኩል ጥበቃም ያደርግላቸዋል፡፡ በሐይማኖቶች መካከል መቻቻልና መከባበር እንዲኖር መድረክ ተግቶ ይሠራል፡፡

1-16- ሀገራችን ከሌሎች አገሮችና መንግስታት ጋር የሚታደርገው ግንኙነት በጋራ ጥቅም፣ በእኩልነት፣ በመከባበርና በእርሰበርስ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ ባለመግባት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ሀገራችን ከጎረቤቶችዋ ጋር ያላትን ድንበሮች ሁሉ በሚገባ ለመለየት ከሚመለከታቸው ጎረቤት ሀገሮች ጋር በአጠቃላይ ድርድር ይካሄዳል፡፡ በዚህም መሠረት በአሁኑ ወቅት በአማራና በጋምቤላ ክልላዊ መነግሥታት አከባቢዎች ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ሳይቋጩ የቆዩ የድንበር ጉዳዮች ፍትሐዊ መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ድርድሩም ለሕዝባችን ግልጽ ሆኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታውቆና ይሁንታ አግኝቶ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

1-17- የሀገራችንን ጥቅሞችና መብቶች ለሌላ ወገን አሳልፈው የሚሰጡትን ስምምነቶች የማንቀበል ሲሆን በተለይም የአልጀርስ ስምምነትንና የባሕር በር ባለቤትነት ጉዳይ እንደገና ድርድር እንዲካሄድበትና በአግባቡ መብታችንንና ጥቅማችንን በሚያስከብር መልኩ መፍትሄ እንዲያገኝ መድረክ ያለመታከት ይታገላል፡፡

## ክፍል 2- የዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች አከባበርን በሚመለከት፡-

2-1- የዜጎች በነፃነት ሀሳብን የመግለጽና መረጃን የማግኘት መብትን በሚመለከት በሕገመንግሥቱ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በትክክል ሳይዛነፉና ሳይሸራረፉ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ እነዚህን ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌዎች በሚጻረር መልኩ የወጡ ሕጎችም ይሻራሉ፡፡

2-2- በፕሬስም ሆነ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች ጠንካራ የግል ሴክተር ተሳትፎ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የመንግሥት የመገናኛ ብዙሃንም ከገዥው ፓርቲ ፖለቲካ አመለካከት መጥመቂያ መሣሪያነት ተላቀው በሕገመንግሥቱ በተደነገገው መሠረት ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ሁሉንም አስተያየቶችንና አመለካከቶችን በእኩልነትና በፍትሐዊነት ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ ይመራሉ፡፡ ተቋማቱን ለመምራት የሚሾሙት ሰዎችም ለዚሁ ሀገራዊ ሀላፊነት የሚመጥን ሙያዊ ብቃት ያላቸውና ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ለትምህርት ማሠራጫ የሚቋቋሙ የመገናኛ ዘዴዎችም ለገዥው ፓርቲ የፖለቲካ አላማ ማሰራጫነት መዋላቸው ቀርቶ ለተቋቋሙለት የማስተማር ዓላማ ብቻ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

2-3- በሀገራችን ዜጎችና የሌሎች ሀገሮች ዜጋ የሆኑ ሕጋዊ ነዋሪዎች በኢንተርኔትና በቴሌፎን በመጠቀም የሚፈልጉትን መረጃ ያለአንዳች ስጋት በነፃነት የሚያገኙበትና የሚለዋወጡበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በእነዚህ መገናኛ ዘዴዎች አማካይነት የዜጎችን የግል ነፃነት ለማፈን

በገዥው ፓርቲ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ማለትም እንደ ጃሚንግ፣ የኢንተርኔት ጣቢያ አፈናና የስልክ ጠለፋ የመሳሰሉት ሕገ ወጥ ተግባራት እንዲቀሩ ይደረጋል፡፡

2-4- ሀሳብን ከመግለጽ ነፃነት ጎን ለጎን የሀገር ነፃነትና ጥቅም የማስጠበቅ፣ የሕዝብን ባሕልና ወግ የማስከበር፣ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ክብርና ነፃነት ቀናኢ የመሆንና የሌሎች ወገኖች ነፃነትና መልካም ስምም ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

2-5- ነፃና ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ ያላቸው፣ ለአባሎቻቸው መብትና ጥቅም፣ ለዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የሚታገሉ ድርጅቶች በሀገራችን መኖርና በነፃነት መንቀሳቀስ መቻል ሀገራችንን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገርና የዜጎችን መብትና ነፃነት ለማስከበር ወሳኝ መሆናቸውን መድረክ በጽናት ያምናል፡፡ በመሆኑም በሕገመንግሥቱ የተደነገገው የመደራጀት መብት ያለአንዳች መሰናከል እንዲከበርና በነፃነት በመደራጀት መብት ላይ ሳንካ ለመፍጠር የሚወጣ ሕግም ሆነ አሰራር እንዳይኖር ይደረጋል፡፡

2-6- ማንኛውም ዜጋ ሃሳቡንና ፍላጎቱን ከሌሎች ጋር በሰላማዊ መንገድ ለመተግበር በሙያ፣ በፆታ፣ በዕድሜ እና በመሳሰሉት የብዙሃን ማሕበራትና እርሱ የሚፈልገውን አመለካከት በሚያራምድ የፖለቲካ ፓርቲ የመደራጀት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

2-7- የፖለቲካ ፓርቲ ያልሆኑ ድርጅቶች በፖለቲካ ጉዳይ አቋም ለመውሰድ ሳይገደዱ በነፃ ሕዝባዊ ድርጅትነት ለቆሙለት ዓላማና ላቋቋሙዋቸው አባላት መብት የመቆምና የመከራከር መብት አላቸው፡፡ በዚሁም መሠረት የሙያ፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የገበሬዎችና የንግዱ ማሕበረሰብ ማሕበራት በሙሉ ከገዥው ፓርቲና ከመንግሥት ጥገኝነትና ተጽኖ ነፃ ሆነው በሲቪክ ማሕበርነታቸው ለአባሎቻቸው ፍላጎትና ጥቅም እንደዚሁም ለሕግ ብቻ ተገዥ በመሆን እንዲደራጁና እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊው ሁኔታ ይመቻችላቸዋል፡፡

2-8- በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሲቪክ ማሕበረሰብ እና ሌሎች የሕዝብ አደረጃጀትን የሚመለከቱ ሕጎች የመደራጀት መብትን በማይገድብ መልኩ እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡

2-9- ለፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ የብዙሃን ማሕበራት ከመንግሥት የሚቀርብ ድጋፍ ያለአንዳች አድልኦ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ የኢህአዴግ አባላት በመንግሥት ሀብትና ንብረት እየተጠቀሙ የምርጫ ዘመቻም ሆነ በአጠቃላይ አመለካከታቸውን በሕዝብ ላይ የሚጭኑበትና ገዥው ፓርቲ ለራሱ የሴቶችና የወጣቶች ክንፎች መላውን ሴቶችና ወጣቶችን እንደሚወክሉ በማስመሰል የመንግሥትን ሀብት ያለአግባብ እንዲጠቀሙ እያደረገ ያለበት አሰራሮች ሕገ ወጥ ስለሆኑ በአስቸኳይ እንዲቀሩ ይደረጋል፡፡

2-10- ማንኛውም ሰው በሕገ መንግስቱ በተደነገገው መሠረት በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት ይከበርለታል፡፡ እነዚህ መሠረታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ሕገመንገሥታዊ መብት ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ ሕጎችና አሰራሮችም ይሻራሉ፡፡ ሕዝቡ የመሰብሰብና ሰላማዊሰልፍ የማድረግ ሕገመንግሥታዊ

መብቶቹን እንዳይጠቀም አልተፈቀደላችሁም በማለትም ሆነ ወይም ሆነ ብሎ አዳራሽ እንዳያገኙ እንቅፋት በመፍጠር አዘጋጆችንም ሆነ ሕዝቡን በሚያጉላሉ የፌደራልና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣናት ላይም የማያዳግም ሕጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

2-11- የኢህአዴግ መንግሥት በሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎችም ሆነ ሀገራችን ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የተካተቱትን የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በመተላለፍ የሚፈጽማቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡

2-12- በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ፣በአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር፣በአለም አቀፍ የዜጎችና ፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽንና የኮቶኑ ስምምነት የተደነገጉት እነዚሁ መሠረታዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በሁለንተናዊ መልኩ ተከብረው በትክክል ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

2-13- የመንግስት አካላትና ባለሥልጣናት እነዚህን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች አክብረው እንዲሠሩና ሳያከብሩ በቀሩ ጊዜ በሕግ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ተበዳዮችም ለደረሰባቸው በደል የሞራልና የማቴሪያል ካሳ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

2-14- የሰብአዊ መብት ሥራቸውን በብቃት ለማከናወን እንዲችሉ አስፈላጊው የሕግ ድጋፍ እንዲኖራቸውና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመከታተልና ለማጋለጥ በሚያስችላቸው መልኩ ከአስፈጻሚ አካላት ተጽኖ ነፃ ሆነው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡

2-15- በሕግ አስፈጻሚ አካላት ሕገ ወጥ እርምጃ ዜጎች ሕይወታቸውን የሚያጡበት ሁኔታ እንዲቆምና ድርጊቱን የሚፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት ሲያጋጥሙ ተለይተው ለሕግ የሚቀርቡበትና የማያዳግም ሕጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው አግባብ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

2-16- ማነኛውም ሰው ንብረት የማፍራት መብት ስላለው መንግስት ለግል ንብረት ተገቢውን ጥበቃ ያደረጋል፡፡ ስለዚህም ካለራሱ ፈቃድ ወይም ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ ሀብቱና ንብረቱ አይወሰድበትም፡፡ ለሀገርና ለሕዝብ የጋራ ጥቅምና ልማት የግል ንብረትን ለመንግሥት ማስረከብ ቢያስፈልግ ባለንብረቱ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ ካሳ ይሰጠዋል፡፡

2-17- ማንኛውም ሰው የግል ሕወቱ (ግላዊነቱ) የመከበር መብት ያለው ስለሆነ የደህንነት ተቋማት በዜጎች የግል ህይወት ላይ የሚያደርጉት ክትትልና በሕብረተሰቡ ውስጥ የፍርሃት ድባብ ለመፍጠር የሚያደርጉት የዛቻና የማስፈራራት እንቅስቃሴዎች እንዲቆሙ ይደረጋሉ፡፡ የግል መኖሪያ ቤትም ሆነ የሥራ ቦታ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አይበረበርም፡፡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚፈጸመው ብርበራም ከማንኛውም ማስፈራራትና እንግልት በጸዳ መልኩ ይሆናል፡፡

2-18--ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ውጭ ሊያዝና ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት አይታሰርም፡፡ የተያዙ ሰዎች ምርመራ በሚደረግበት ወቅት ድብደባን ጨምሮ ከማንኛውም ኢሰብአዊ ከሆነና ክብርን ከሚያዋርድ ምርመራ የተጠበቁ ይሆናሉ፡፡ በራሱ/ ሷ ላይ እንዲመሰክርም አይገደድም፡፡

2-19- ማንኛውም ሰው በፖለቲካ አመለካከቱ ምክንያት ሊታሰር ስለማይገባ የኢህአዴግ መንግሥት በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ያሰራቸው ወገኖቻችን እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ የተያዙ ሰዎች ወንጀል መሥራታቸው በፍርድ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹሕ እንደሆኑ ስለሚቆጠሩ መንግሥት የተያዙ ሰዎችን ጥፋተኛ ለማሰኘት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያከሄደው የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የተከለከለ ይሆናል፡፡

2-20- የተያዙ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብና በዋስ የመፈታት መብታቸውን የሚጻረር ማንኛውንም እርምጃ መንግሥት አይወስድም፡፡ በእስር ቤት ሲቆዩም ንጽሕናው በተጠበቀና በታወቀ እስር ቤት ብቻ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሀይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸውና ከሕግ አማከሪዎቻቸው ጋር የመገናኘትና እንዲጎበኙዋቸው ዕድል የማግኘት መብታቸውም በትክክል ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ክፍል 3- የኢኮኖሚ ልማትን በሚመለከት፡-

የመድረክ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲ ዋና ትኩረት ሀገራችንን ከኋላ ቀርነት አለቅቆ የበለጸገ ሕብረተሰብ መገንባትና የኢኮኖሚ ልማቱ ዜጎች ያለፖለቲካዊ አድልኦ ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ ኑሮአቸውም በተጨባጭ የሚሻሻልበትና የኑሮ ውድነቱም ጫናዎች የሚቃለሉበት እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በኢህአዴግ አገዛዝ በሚካሄዱት የኢኮኖሚ ልማት ሥራዎች አማካይነት ሕዝባችን ከድህነትና ከኑሮ ውድነት ሰቆቃ የሚላቀቅበት ሁኔታ በተጨባጭ ስላልታየ ይኸንኑ ሁኔታ ከመሠረቱ የሚለውጡ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በኢኮኖሚውም ልማት የእርሻና የእንዱስቱሪ የኢኮኖሚ ዘርፎች እርሰበእርሳቸው በመመጋገብ ሚዛናዊ በሆነ የእድገት ሂደት የሚመሩበት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በዚሁም መሠረት በየኢኮኖሚ ዘርፎችና በመሠረተ-ልማት ረገድ የሚከተሉት አበይት ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

### 3-1- በግብርና ልማት ዘርፍ የሚከናወኑ ሥራዎችን በሚመለከት፡-

3-1-1- አርሶ አደሩ የሚጠቀሚባቸው መሬቶች በራሱ በአርሶ አደሩ የግል ባለቤትነት የሚያዝበትና አርሶ አደሩ ከመሬቱ በፖለቲካዊና ሌሎች የተለያዩ ተጽኖዎች የማይፈናቀልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ የመሬት ግብርም በአርሶ አደሩ አቅም ደረጃ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

3-1-2- በጥናት ላይ የተመሠረተና መሬትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖርና ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

3-1-3- አርሶ አደሩ የተለያዩ የግብርና ግብአቶችን ማለትም ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎችን፣ ማዳበርያና ምርጥ ዘሮችንና የመሳሰሉትን ተገቢው የመንግሥት ድጋፍ ተደርጎለትና ከኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ተጽኖና ጥገኝነት ተላቅቆ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኝበትና ምርታማነቱን የሚያሳድግበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ ግብአቶቹን የሚገዛበት የባንኮች ብድር አግኝቶ የእርሻ ልማቱን የሚያስፋፋበት ሁኔታዎችም ይመቻቻሉ፡፡

3-1-4- የእርሻ ምርምር ሥራዎች በስፋትና በጥራት የሚካሄዱባቸው ተቋማት እንዲስፈፉና የገበሬውን ምርታማነት ከማሳደግ አንጻር ከአድልኦ የጸዳ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። ዘመናዊና የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችን ለገበሬው የሚያቀርቡና ምርታማነቱን የሚያግዙ ፋብርካዎችም እንዲስፋፉ ይደረጋል።

3-1-5- የግብርና ምርት ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ በቂ ምርት ለማምረት እንዲቻል ለመስኖ ልማት በቂ በጀት በመመደብና የመስኖ እርሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ በማድረግ የግል ባለሀብቶችም በመስኖ ሊለሙ በሚችሉ አከባቢዎች በስፋት ተሠማርተው እንዲያመርቱ አስፈላጊው ማበረታቻና አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖር ይደረጋል። መንግሥት ለመስኖ አገልግሎት የሚሰጡ ትላልቅ ግድቦችን እየሠራ ባለሀብቶችና ገበሬዎች ተመጣጣኝ ዋጋ እየከፈሉ እንዲጠቀሙ በማድረግ ዘመናዊ የመስኖ እርሻዎችን የሚያስፋፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

3-1-6- የግብርና ልማት ሠራተኞች ከልማት ሥራቸው ይልቅ ለገዥው ፓርቲ የፖለቲካ ካድሬነት ሥራ ላይ እንዲሠማሩ የተደረገበት ሁኔታ ተወግዶ በገዥው ፓርቲ ከሚፈጸሚባቸው ተጽኖ ነፃ እንዲሆኑ ይደረጋል። በሰለጠኑበት ሙያ በሙሉ አቅማቸው አርሶ አደሩን ስለግብርና ልማት በማስተማር አገልገሎት የሚሰጡበት በየጊዜው የሙያ ብቃታቸውን በትምህርትና በስልጠና የሚያሻሽሉበትና ተመጣጣኝ ክፍያና እድገት የሚያገኙበት ሁኔታም ይመቻችላቸዋል።

3-1-7- የግብርና ልማቱ ሀገራችን በምግብ እራሷን እንድትችል የሚያደርጋት እንዲሆን የምግብ ምርት በከፍተኛ ትኩረት እንዲመረት ይደረጋል። ዘመናዊ እርሻዎችም በዚህ ረገድ ድርሻቸውን እንዲወጡ ይበረታታሉ።

3-1-8- የአርብቶ አደሩ የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማፋጠን የመኖ፣ የውሃና የእንስሳት ጤና ችግሮችን ለመፍታት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

3-1-9- የእንስሳት ሀብት ልማቱ በቁጥር ላይ ከሚያተኩረው ኋላ ቀር የከብት እርባታ ዘዴዎች ተላቆ በጥራትና ከፍተኛ ምርታማነትን ሊያስገኝ ወደ ሚያስችል ዘመናዊ የእርባታ ዘዴዎች እንዲሸጋገር አስፈላጊው የስልጠናና የማበረታቻ ድጋፎች ለአርብቶ አደሩ ሕዝብ ይሰጣሉ። የልማቱ እንቅስቃሴም አርብቶ አደሩን ሕዝብ በስፋት ያሳተፈና በፍላጎቱ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

3-1-10- የአርብቶ አደሩ መሬቶች የአከባቢው ሕብረተሰብ የጋራ ሀብት ሆነው በአከባቢው ሕዝብ ስምምነት መሠረት በጥቅም ላይ ይውላሉ።

3-1-11- በእርሻም ሆነ በከብት እርባታ ረገድ የሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ለሀገራችን የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ለሀገራችን የእንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የማቅረብ ድርሻቸውን ለመወጣት እንዲበቁ ተገቢው አመራርና ድጋፍ ይሰጣል።

3-1-12- የሀገራችን ባለሀብቶች በሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎች ልማት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። ለውጭ ባለሀብቶች የሚሰጡ ሰፋፊ እርሻዎች ለሀገራችን ተገቢውን (apropriete) ዘመናዊ

ቴክኖሎጂዎችን የሚያስተዋውቁ፣ ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ የሚያስችሉ፣ የአርሶ አደሩን የመሬት ይዞታ የመንጠቅ (land grabing) ሥራ የማያካሄዱ፣ ለሀገራችን ልማት የሚውል ተመጣጣኝ የሊዝ ክፍያ የሚፈጽሙና የአከባቢ ብክለትን የማያስከትሉ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

## 3-2- የእንዱስትሪ ልማትን በሚመለከት፡-

3-2-1- ለሕብረተሰባችን የሚያገለግሉ የፍጆታ እቃዎችና የማምረቻ መሣሪያዎችን እንደዚሁም ለሀገራችን የውጭ ምንዛሪ የሚስገኙ ምርቶችን በብዛትና በጥራት የሚያመርቱ እንዱስትሪዎች በሀገራችን እንዲስፋፉና በአሁኑ ወቅት ከሀገራችን አጠቃላይ ምርት መጠን እንዱስትሪው ያለው ዝቅተኛ ድርሻ በተቻለ ፍጥነት እንዲያድግ በዚሁም ሂደት ወደ እንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገው ሽግግር እንዲፋጠን ተገቢው ትኩረትና ማበረታቻ ይደረጋል፡፡

3-2-2- የእንዱስትሪ ልማቱ ለሀገራችን የሚያስፈልገውን ቁሳዊ ምርት ከማስገኘት ባሻገር ለዜጎቻችን ከፍተኛ የሥራ ዕድል በመፍጠርና አሁን ያለውን የሥራ አጥነት ችግሮችን በማቃለል ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

3-2-3- ለእንዱስትሪው ልማት ዋና መሠረት የሚሆነው የሣይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ይስፋፋል፡፡

3-2-4- የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በእንዱስትሪው ልማት ሥራዎች በስፋት እንዲሳተፉ ተገቢው ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፡፡

3-2-5- በመንግሥት እጅ የሚገኙ እንዱስትሪዎች ወደ ግል ባለሃብቶች ተዛውረው በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተጠናክረው በሀገሪቷ ኢኮኖሚ እድገት ተገቢውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

3-2-6- የእንዱስትሪው ልማት ለእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ግብአት የሚሆኑ ምርቶችን በማምረትና የእርሻ ምርቶችን ደግሞ በግብአትነት የሚጠቀም እንዲሆን በማድረግ ሁለቱ ክፍለ ኢኮኖሚዎች የፊትና የኂላ ግንኙነት በመፍጠር (ተመጋጋቢ በመሆን) ለልማታችን መፋጠን የሚተጋገዙ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## 3-3- የውሃ ሀብትና፣የማዕድን ልማት ሥራዎችን በሚመለከት፡-

3-3-1- የሀገራችን የውኃ ሀብት በተቀናጀና በተጠና መንገድ በከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ ይውላል፡፡ በዚሁም መሠረት የዝናብ ጥገኛ በሆነው የግብርና ሥራችን ምክንያት ካለንበት የረሃብ ችግር ለመላቀቅና ራሳችንን በምግብ ለመቻል ወንዞቻችንን በመገደብና የከርሰምድር ውኃን ጥቅም ላይ በማዋል የውኃ ሃብታችን የግብርና ልማት ሥራችንን በሚያግዝ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች ግንባታም የመስኖ ልማትን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በስፋት ይከናወናል፡፡

3-3-2- የወሰን ተሻጋሪ ወንዞቻችንን አጠቃቀም በሚመለከት በተለያዩ የጎረቤት መንግሥታትና በሀገራችን መካከል የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በአግባቡ የሚያስጠብቁና ለሀገራችንም ሆነ ለጎረቤቶቻችን ፍትሐዊ የውኃ ሀብት አጠቃቀም የሚያረጋግጡ ድርድሮች ይካሄዳሉ፣ ስምምነቶችም ይፈረማሉ፡፡ ኢትዮጵያ የአባይም ሆነ የሌሎች ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች መፍለቂያ እንደመሆኑዋ መጠን ወንዞቹን በማልማት የሚገባትን ያህል ድርሻዋን የመጠቀም ተፈጥሮአዊ መብት ያላት ስለሆነ በድህነቱዋ በማሳበብም ሆነ በኃይል በማስፈራራት የተጠቃሚነት መብቷን የሚጻረር አካሄድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህም ከግንዛቤ ማጣትም ሆነ የራስን ጥቅም ብቻ ከማራመድ የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዳይከሰቱ እየተከላከልን መሠረታዊ የሕዝባችንን ጥቅም አሳልፈን ሳንሰጥ ለፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነትና የጋራ ልማት የበኩላችንን ጥረት እናደረጋለን፡፡ ወንዞቹም ለቅራኔዎች ሳይሆን ለትብብርና ለጋራ ልማት እንዲሁም ለመልካም ግንኙነቶች መሠረት እንዲሆኑ መድረክ ጠንክሮ ይሠራል፡፡

3-3-3- እያደገ የሚሄደውን የእንዱስትሪ ልማት ሥራ የኃይል ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ለማሟላት እንዲቻል ለኃይል ማመንጨት ሥራ በቂ በጀት በመመደብና የሰው ኃይል በማሰልጠን ሀገራችን ያላትን አማራጭ የኃይል ምንጮች ጥቅም ላይ እንድታውል ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡ አማራጭ የእነርጂ (የኃይል) ምንጮችን ለማስፋፋት ተገቢው ጥናት ይደረጋል፡፡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የጋዝ፣የነፋስ፣የፀሐይ፣የባዮጋዝና የጂኦቴርማል የኃይል ምንጮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋሉ፡፡

3-3–4- በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ እየተመረተ ያለውንም የኤሌክትርክ ኃይል በአግባቡ ለሕብረተሰቡ አገልግሎትና ለሀገራችን ልማት ማዋል ስለተሳነው የምርት ተቋማት፣ መስሪያ ቤቶችና መኖሪያ ቤቶች ወዘተ… የኃይል መቋረጥ ችግር እያጋጠማቸው ይገኛል፡፡ መድረክ የሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል በቅድሚያ ለሀገራችን ፍላጎት ማሚያ እንዲውል በማድረግ በኢህአዴግ የተፈጠሩትን ሰው ሠራሽ ችግሮች ከመሠረቱ ያስወግዳል፡፡

3-3-5-ንጹሕ የመጠጥ ውኃ እስከአሁን ያልደረሳቸው ወገኖቻችንም እንዲደርሳቸው ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡

3-3-5- የውኃ ሀብት ልማት ባለሙያዎች አቅማቸው እንዲጎለብት በከፍተና ደረጃ እንዲሰለጥኑና ልምድ እንዲቀስሙ አስፈላጊው ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

3-3-6- የውኃ ሀብታችን ከብክለት እንዲጠበቅ አስፈላጊው የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ይከናወናሉ፡፡

3-3-7- የሀገራችን የማዕድን ሀብት በትክክል እንዲታወቅና ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲውል ለማድረግ በቂ በጀት በመመደብና ጥናት በማካሄድ የተሟላ የጂኦሎጂካል ካርታ ይሠራል፡፡

3-3-8- እስከአሁን የታወቁት የማዕድን ሀብቶቻችን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባለሀብቶች ተሳትፎ ይለማሉ ጥቅም ላይም ይውላሉ፡፡

3-3-9- ለሀገራችን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ከፍተኛ የማዕድን ሀብቶች ማለትም ወርቅ፣ነዳጅ እና የመሳሰሉት በሚገኙባቸው አከባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች ከማዕድን ልማቱ ልዩ ጥቅም (የሮያሊቲ መብት) እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 3-4- የትራንስፖርትና የመገናኛ አገልግሎቶችን ልማት በሚመለከት፡-

3-4-1- የሀገር ውስጥና የአከባቢያዊ የልማት ትስስሮችን ለማስፋፋት እንዲቻል ክልሎችን ከክልሎች የሚያገናኙና ከጎሮቤት ሀገሮችም ጋር ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የሚያግዙ ትላልቅ አውራ ጎዳናዎች በጥራት እንዲሠሩና እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

3-4-2- በሀገር ውስጥና ከጎሮቤት ሀገሮች ጋር የሚደረገውን የንግድ እንቅስቃሴ የበለጠ ለማጠናከር የባቡር መሥመር መገናኛ ዘዴዎች ይስፋፋሉ፡፡ የባቡር መሥመሮቹ ዘመናዊና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚጠቀሙ ባቡሮችን አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሆነው ለኢኮኖሚ ልማታችንም ያላቸው ጠቀሜታ እየተገመገመ በቅድም ተከተል ይሠራሉ፡፡

3-4-3- የገጠሩ ሕብረተሰብ ምርቶቹን በቀላሉ ለገበያ ለማቅረብ እንዲችልና የግብርና ግብአቶችንና የፍጆታ ዕቃዎችን በቀላሉ ለማግኘት እንዲችል ከተሞችን ከገጠሩ ሕብረተሰብ ጋር የሚያገናኙ የገጠር የመኪና መንገዶች በስፋትና በጥራት ይሠራሉ፡፡

3-4-4- የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት ተገቢ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ የግል ባለሀብቶችም በአየር ትራንስፖርት አገልገሎት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፡፡

3-4-5- የቴሌኮሙኒኬሽንና የፖሰታ አገልግሎቶችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፉና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት እንዲበቁ የሚያስችሉ የማስፋፋት ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

## 3-5- የፋይናንስ ተቋማት ልማትን በሚመለከት፡-

3-5-1- በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተጀመሩት የባንክ አገልግሎቶች ይበልጥ እንዲስፋፉ ተገቢው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

3-5-2- የረጅም ጊዜ የልማት ሥራ ለሚያከናውኑ ባለሀብቶች የረጅም ጊዜ ብድር የሚያቀርቡ የልማት ባንኮች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ይበረታታሉ፡፡

3-5-3- በገጠርም ሆነ በከተሞች ለሚኖሩና በአነስተኛ የገቢ ማስገኛ የሥራ ዘርፎች ለመሠማራት ለሚፈልጉ ዜጎች በተመጣጣኝ ወለድ ብድር እንዲያቀርቡ እየተደራጁ ያሉት የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ከወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ለሁሉም ዜጎች እኩልና ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት በሚችሉበት መልክ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

3-5-4- በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከትም ለሀገራችን ዘላቂ ልማት ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር እንቃስቃሴያቸው እየተጠና ሥራ ላይ የሚውልበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 3-6- የከተሞች ልማትን በሚመለከት፡-

3-6-1- የከተማ ነዋሪዎች ለመኖሪያና ለልማት በሚጠቀሙበት መሬት ላይ የባለቤትነት መብታቸውን በማስጠበቅ ከይዞታቸውና ንብረታቸው ከሕግ አግባብ ውጭ የሚነሱበት ሁኔታ እንዲቆም ይደረጋል፡፡ በሕግ አግባብ ሲነሱም በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመን (ከሊዝ ዋጋ ጋር የሚመጣጠን) ካሳ ይከፈላቸዋል፡፡

3-6-2- አቅም ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤቶችን በግልም ሆነ በጋራ ለመሥራት እንዲችሉ ተገቢው ድጋፍና ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፡፡ የሞርጌጅ ባንክ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታም ይመቻችላቸዋል፡፡ አቅም ለሌላቸው ዜጎች ደግሞ ከሙሰኝነት በጸዳ መልኩ በመንግስት እየተሠሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ያለአድልኦ የሚከራዩና የሚሸጡ ቤቶች ሥራ በስፋት ይከናወናል፡፡

3-6-3- በኢህአዴግ ሥርዓት ተስፋፍቶ የሚገኘው የከተማ ቦታ በፓርቲ አባልነት፣ በዝምድናና በተለያዩ የጥቅማጥቅም ግንኙነቶች የሚከፋፈልበት አሠራር ተወግዶ የከተማ መሬት ግልጽና ከሙስና በፀዳ ሁኔታ እንደዚሁም ተጠያቅነትን በተላበሰ መንገድ የሚተዳደርበት ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

3-6-4- በየከተሞች ያሉት የመንግሥትና የቀበሌ ቤቶች ለልማት ሲፈርሱ አበል ሲያገኙ ለነበሩ ዜጎች ተገቢው ክፊያ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመን ይደረግላቸዋል፡፡ ተከራዮችም እንደአቅማቸው ሌላ የመንግሥት ቤት በመከራየት ወይም የራሳቸው መኖሪያ ቤት በመሥራትና በመግዛት ተለዋጭ መጠለያ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል፡፡

3-6-5- የከተሞች ልማት በፕላን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በከተሞች ልማት ምክንያት ከከተሞች አከባቢ የሚፈናቀሉ አርሶ አደሮች ወይም ሌሎች ዜጎች ከልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውና ኑሮአቸውን ለማሻሻል የሚያበቃቸው በቂ ካሳ (ከሊዝ ጋር የሚመጣጠን) እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3-6-5- በመሬት ጥበትና በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት ወደ ትላልቅ ከተሞች ለሚፈልሰው የሰው ኃይል በአከባቢያቸው ከተሞች ሊሠማሩባቸው የሚችሉባቸውን የሥራ መስኮች በመፍጠር ላይ ያተኮረ ስትራቴጂና ስልት ተቀይሶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የገጠር ከተሞችን (የወረዳና የዞን ከተሞችን) የአነስተኛ እንዱስትሪና የልማት ማዕከላት የማድረግ ሥራዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡

## 3-7- የአከባቢ ጥበቃና የቅርሶችና ብሔራዊ ፓርኮች እንክብካቤን በሚመለከት፡-

3-7-1- የግብርና ልማት ከማስፋፋት ጎን ለጎን የደን ሀብታችንም እየተመናመነ እንዳይሄድና የደን ልማት ሥራም እንዲስፋፋ ሕብረተሰቡና የግል ባለሀብቶች በስፋት እንዲሠማሩበት የማስተባበር ሥራዎች ይሠራሉ፣ ተገቢው ማበረታቻም ይደረግላቸዋል፡፡ እየተመናመነ በመሄድ ላይ ያለው የደን ሀብታችን ጨርሶ ከመውደሙ በፊት የምንከባከብበትንና የምንተካበትን ስተራቴጂ በመቀየስ የተቀናጁ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ፡፡ የሀገራችንን ሕዝብ በኤሌክትርክና

ሌሎች ታዳሽ የማገዶ ምንጮች የሚሠሩ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ በደን ሀብታችን ላይ እየደረሰ ያለውን ውድመት ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ የደን ልማትን ስራዎች በመንግሥት በሕብረተሰቡና በግል ባለሀብቶች ሰፊ ተሳትፎ እንዲካሄዱ የተቀነቀጁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

3-7-2 የእንዱስትሪ ልማት ሥራዎች በአከባቢው ሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱና የአከባቢ ብክለት እንዳያስከትሉ ተገቢው የመከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዚሁም መሠረት የእንዱስትሪና የቤት ፍሳሾችን የመጣራትና የማስወገድ ስራዎች በዘመናዊ መንገድ እንዲከናወኑ ይደረጋል፡፡ የአከባቢው ሕዝብ ከእንዱስትሪ ልማቱ ተጠቃሚነቱ እንዲረጋገጥም ይደረጋል፡፡

3-7-2- የደን ልማቱ ሥራ ትርፋማና ሳቢ እንዲሆን የደን ሀብታችንን የሚጠቀሙ እንዱስተሪዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የደን ውጤቶችን የሚጠቀሙ የተለያዩ መድኃኒቶች እንዲመረቱም መድረክ ትኩረት ሰጥቶ ያበረታታል፡፡

3-7-3- የደን ሀብት ባለሙያዎች በብቃትና በጥራት እንዲሰለጥኑና ለደን ልማት እንቅስቃሴዎች ሙያዊ እገዛ እንዲያደርጉ በትኩረት ይሠራል፡፡

3-7-4- ሀገራችን የበርካታ ጥንታዊ ቅርሶችና መስሕቦች ባለቤት ስለሆነች እነዚህ መተኪያ የሌላቸው ሀብቶች ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3-7-5- ብሔራዊ ፓርኮቻችን የበርካታ ብርቅዬ እንስሳትና እጽዋት መጠሊያና መገኛ ስለሆኑ ከማናቸውም አይነት ጉዳት እንዲጠበቁ ይደረጋል፡፡ በዚሁም የቱርስት እንዱስትሪ እንዲስፋፋና የአከባቢው ሕብረተሰብም ከእንዱስትሪው መስፋፋት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 3-8- መንግሥት በኢኮኖሚ ልማት የሚኖረውን ሚና በሚመለከት፡-

3-8-1- በተለያዩ አከባቢዎች ለሚካሄዱት የኢኮኖሚ ልማት እንቃሴዎች መስፋፋት የሚያግዙ የተለያዩ መሠረተ ልማት ሥራዎች በመንግስት ይሠራሉ፡፡ በዚሁም መሠረት የመንገድ ሥራ፣ የባቡር መስመሮች ዝርጋታ፣የመብራት፣ የውኃ፣ የቴሌፎን፣ የአየር ማረፊያ፣ የፋይናንስ ተቋማት ወዘተ... አገልግሎቶችን ለተለያዩ አከባቢዎች በፍትሐዊነት በማዳረስ ለሁሉም ክፍለ ኢኮኖሚዎች እድገት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሥራዎች ይከናውናሉ፡፡

3-8-2- በአሁኑ ወቅት ገዥው ፓርቲ በኢኮኖሚው ዘርፍ በሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ላይ ተጽኖ በማድረግና ከገዥው ፓርቲ ጋር ቁርኝት ላላቸውና ለአባላቱ በማዳላት በተለየ ሁኔታ እንዲጠቀሙ የሚያደርጋቸው አድሎአዊ አሠራሮች እንዲቀሩ ይደረጋል፡፡ ሁሉም የሀገራችን ባለሀብቶች በእኩልነትና ያለአድሎ አቅማቸው በፈቀደ መጠን በነፃ ገበያ መርሕ መሠረት በልማት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፡፡ ከገቢያቸው ጋር የተመጣጠነ ግብርም እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

3-8-3- የሀገራችን ባለሀብቶች ከሌላው ዓለም ባለሀብቶች ጋር ተወዳዳሪ ሆነው የሚወጡበትና የልማት ተነሳሽነታቸው የሚጎለብትበት ሁኔታ ተጠንቶ ተገቢው ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፡፡

የውጭ ባለሀብቶችም የሀገራችን ባለሀብቶች ሊሸፍኑዋቸው በማይችሉባቸው ከፍተኛ የልማት ዘርፎች እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፡፡

3-8-4- መንግሥት ለዘላቂ ልማታችን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸውና የግል ባለሃብቶች ደፍረው በማይሳተፉባቸው ከባድ እንድስትሪዎች ልማቶች ላይ ይሳተፋል፡፡

3-8-5- ገዥው ፓርቲ በአሁኑ ወቅት እንደውመንትና ሌሎች የተለያዩ ስሞችን እየሰጠ ከሚያንቀሳቅሳቸው የኢኮኖሚ ተቋማት እጁን እንዲያስወጣ ይደረጋል፡፡ ማነኛውም ፓርቲም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሀብት ማፍሪያ ተቋም ባለቤት አይሆንም፡፡

3-8-6- በሀገራችን እየተባባሰ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ንረትና የሀገራችን ገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም ችግሮችን በአስቸኳይ ለማስወገድ የሚያስችል እርምጃ ይወሰዳል፡፡

## ክፍል 4-የማሕበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት፡-

### 4-1-የሥራ አጥነት፣የድህነትና የፍልሰት ችግርን በሚመለከት፡-

4-1-1- በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተስፋፋ ያለውን የሥራ አጥነት ችግር በዘላቂነት ለማስወገድ ለዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ የሥራ መስኮችን ማስፋፋት ወሳኝ ጉዳይ ስለሆነ ዜጎች በአንስተኛ እንዱስተሪዎችና የእደጥበብ የሥራ ዘርፎች ተሠማርተው ለራሳቸውና ለሌሎችም የሥራ ዕድል ፈጣሪዎች እንዲሆኑ በሙያ ስልጠናና በማይክሮ ፋይናንስ ረገድ በመንግሥት አማካይነት አስፈላጊው ድጋፍ ይሠጣቸዋል፡፡- በመሬት ጥበትና በአድሎአዊ አስተዳደር ምክንያት በአሁኑ ወቅት በገጠርም የሥራ አጥነት ችግር እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ስለሆነ የአነስተኛ እንዱስትሪና የእደጥበብ የሥራ ዘርፎች በመላው የገጠር ከተማዎችና አከባቢዎችም እንዲስፋፉና እንዲዳረሱ ይደረጋል፡፡

4-1-2- ገዥው ፓርቲ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተባባሰ የመጣውን የዜጎች የሥራ አጥነት ችግር እየተጠቀመ ሥራ የማግኘት ዕድልን ለፓርቲ አባልነትና ደጋፊነት መመልመያ መሣሪያ አድርጎ እየተጠቀመበት ስለሆነና አባልና ደጋፊው ያልሆኑትን በመንግሥት ሥራ ላይ ያሉ ዜጎችን በሰበብ አስባቡ እያፈናቀለ የሥራ አጡን ቁጥር ክፉኛ እያባባሰው ስለሆነ ይህ አድሎአዊ አሠራር በአስቸኳይ የሚቆምበት እርምጃ ይወሰዳል፡፡ በዚሁም መሠረት ሥራ የማግኘት ዕድል ከሙያ ብቃትና ችሎታ ጋር እንጂ በምንም መልኩ ከፖለቲካዊ አመለካከት ጋር ግንኙነት አይኖረውም፡፡

4-1-3- የሀገራችን ዜጎች በሀገራችን ሰፍኖ በሚገኘው አድሎአዊ የኢህአዴግ አሰተዳደርና የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት እየተባባሰ በመጣው የኑሮ ችግር የተነሳ ባሉበት አከባቢና በሀገራቸው ሠርተው ለመኖር ባለመቻለቸው ለአሰቃቂና አዋራጅ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገሮች የስደት ኑሮ እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ይህንን አሰከፊ ሁኔታ በአስቸኳይ ለማስወገድ ፍትሐዊና መልካም አስተዳደርን በማስፈንና የሥራ እድሎችን በመንግሥትና በግል ባለሀብቶች አማካይነት በከተማና በገጠርም በማስፋፋት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በውጭ ሀገሮች

ለሚኖሩ ዜጎቻችን ሰብአዊና ሕጋዊ መብቶች መከበር የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡ በዚሁም መሠረት ከሠራተኛ ተቀባይ ሀገሮች ጋር ስምምነት በመፈራረምና ሲምምነቱ ተጥሶ ቢገኝ በዓለም አቀፍ ሕግ በመዳኘት የዜጎቻችንን መብቶች የማስከበር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

4-1-4- በተደጋጋሚ በተፈጥሮ አደጋ የሚጠቁና አስከፊ ድህነት ውስጥ የሚገቡ ወገኖቻችንን በሀገር ውስጥና ባሉበት አከባቢ የልማት ድርጅቶች ተስፋፍተው በነዚያ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩባቸውን የሥራ መስኮችና የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር እራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል፡፡

<u>4-1-5</u>- ለድህነት ቅነሳ ከዓለም ማሕበረሰብ ለሀገራችን የሚደረገው ዕርዳታ የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠርና ለዘላቂ ልማትና ዕድገት እንዲውል ይደረጋል፡፡ ገዥው ፓርቲ ይህንኑ ድጋፍ ከራሱ እንደመጣ አድርጎ በማቅረብ ለአባላትና ደጋፊዎች መመልመያነት እየተጠቀመበት ያለው አሠራር ሕገወጥ በመሆኑ በአስቸኳይ ቆሞ ሁሉም በድህነት ውስጥ የሚገኝ ዜጋ እኩል የዕድሉ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ድህነትን ለመቀነስና የሥራ ዕድሎችን ለማስፋፋት የሚከናወኑ ሥራዎች ደረጃ በደረጃ ከውጭ ዕርዳታ ጥገኝነት እንዲላቀቁ ለማድረግ መንግሥት አስፈላጊ በጀት መድቦ የዜጎችን የራስ አገዝ ጥረቶችን የሚደግፍበት አሰራር ተቀይሶ ሥራ ላይ ይውላል፡፡ በሀገራችን በተደጋጋሚ የሚከሰቱት የተፈጥሮ አደጋዎች በተላይም አርሶ አደሮችና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎቻችንን ለኪሳራ እየዳረጉ መሆናቸው ድህነትን እያሰፋው ስለሆነና ለማዳበሪያ ለምርጥ ዘርና ለመሳሰሉት ጉዳዮች የሚበደሩዋቸውን ብድሮች ለመክፈል በማይችሉበት ችግር ውስጥ እየከተታቸው ስለሆነ የተፈጥሮ አደጋ ችግር የሚያጋጥማቸው ዜጎች በዓለም አቀፍ አበዳሪ ሀገሮችና የፋይናንስ ተቋማት ለሀገራችን የሚሰጠው የእዳ ስረዛ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ተቀየሶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## <u>4-2- ትምህርትን በሚመለከት፡-</u>

4-2-1- በኢህአዴግ አገዛዝ የሀገራችን የትምህርት አስተዳደር በሙያ ብቃት ላይ መመሠረቱ ቀርቶ በሹመት በሚሰየሙ የገዥው ፓርቲ ታማኝ ካድሬዎች እንዲመራ መደረጉ፣ የ2ኛ ደረጃና የኮሌጅ የትምህርት ጊዜ እንዲቀነስ መደረጉ፣ ተገቢ ስልጠና ያለቸው በቂ መምህራን አለመኖራቸውና በየትምህርት ተቋማቱ አስፈላጊ የፋይናንስና ቁሳዊ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽኖ እያደረጉ ስለሆነ በእነዚሁ ችግሮች ላይ አስቸኳይ የማስተካከያ የእርምት እርምጃዎችን በመውሰድ ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በዚሁም መሠረት የትምህርት ተቋማቱ የአካዳሚክ ነፃነታቸው ተጠብቆ የሚሠሩበትና ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ስልጠናና ክህሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

4-2-2- መምህራን ነፃ ማሕበራቸውን መሥርተው መብታቸውን የሚያስጠብቁበትና በመማር ማስተማር ሂደት ገንቢ አስተዋፆ ማበርከት የሚችሉበት ሁኔታም ይመቻቻል፡፡ የመምህራን ስልጠና በጥራትና በተከታታይ የሚሰጥበትና የሙያ ብቃታቸው በየጊዜው የሚሻሻልበት ሁኔታ እንዲመቻችም ይደረጋል፡፡

4-2-3- በሀገር ውስጥ በመንግሥት የሚሰጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ዕርዳታ ሰጭዎች የሚሰጡ ነፃ የከፍተኛ ትምህርት ዕድሎች ተጠቃሚዎች የገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች እንዲሆኑ መደረጉ የትምህርት ዕድልንም ለገዥ ፓርቲ አባልነት መመልመያ መሣሪነት እንድውልና በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥም አድሎአዊነት ሥር እንዲሰድ እያደረገ ስለሆነ ይህ አድሎአዊ አሰራር ቀርቶ ሁሉም ዜጋ በእኩልነትና በነፃ ውድድር ብቻ እድሉን የሚያገኝበት አሠራር ተቀይሶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

4-2-4- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አሁን እንደሚደረገው በብዛት መስፋፋት ብቻ ሳይሆን የዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ በበቂ ጥራትና ብቃት ላይ ተመሥርተው የሚያድጉበትና የሚስፋፉበት እንዲሁም ከየትምህርት ተቋማቱ የሚመረቁ ባለሙያዎች የቀሰሙትን ትምህርት በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ራሳቸውንና ሀገራቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊያገለግሉ የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በዚሁም መሠረት በአሁኑ ወቅት ገዥው ፓርቲ የተማረ የሰው ኃይልን ለከፋ የሥራ አጥነት እየዳረገና ውጤታማ ባልሆኑና አነስተኛ ስልጠና ብቻ ያገኙ ዜጎች ሊሠሩ በሚችሉባቸው የሥራ መስኮች እንዲሠማሩ እያስገደደ የሚገኝበት ሁኔታ ተወግዶ ሙያና ባለሙያ ተገናኝተው ውጤታማ ሥራ የሚሰራበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

4-2-3- የ1ኛና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት በብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዎች በወጥነት እንዲሰጥ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሠጣል፡፡ በአሁኑ ወቅት በፌዴራልና በዓለም ዓቀፍ ቋንቋዎች ትምህርት ላይ ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱ ተማሪዎችን እየጎዳ ስለሆነ የፌደራል መንግሥትና ዓለም አቀፍ የሥራ ቋንቋዎችም በየትምህርት ቤቶች በአግባቡ እንዲሠጡ ይደረጋል፡፡

4-2-4- የጎልማሶች ትምህርት በገጠርና በከተማዎች እንዲስፋፋ በማድረግ ሰፊው አርሶ አደርና ሠራተኛው ሕዝብ ከማህይምነት እንዲላቀቅና የሙያ ክህሎት አግኝቶ ምርታማነቱን እንዲያሳድግ በመንግስት አሰፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

4-2-5- የግል የትምህርት ተቋማትም የትምህርት ጥራታቸው ደረጃን የጠበቀ እንዲሆንና በንግድ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ትውልድን በእውቀት የማነጽ ሃላፊነት እንዲወጡ ለማድረግ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

### 4-3- የጤና አገልግሎትን በሚመለከት፡-

4-3-1- ተከታታይነት ያላቸው በሽታን የመከላልና የቁጥጥር ተግባራት ይከናወናሉ፣ ለአክሞ ማዳን አገልግሎትም በቂ ትኩረት በመስጠት የጤና ተቋማት ብቃት ባላቸው የባለሙያ፣ የጤና መገልገያ መሣሪያዎችና የመድኃኒት አቅርቦት ይደራጃሉ፡፡ በተለያዩ የሀገራችን አከባቢዎች ፍትሐዊ ተደራሽነት እንዲኖራቸውና የጤና አገልግሎቶቹም የሙያ ሥነ ምግባር በሚያዘው መሠረት መከናወናቸው እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ ዜጎች የጤና እንሹራንስ የሚያገኙበት ሁኔታም ይመቻቻል፡፡ የሕክምና ባለሙያዎችም ለሚያበረክቱት አገልግሎት የሚመጥን ክፍያ እንዲሰጣቸውና ለሥራቸው አመቺ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

4-3-2- በገጠርም ሆነ በከተማ አከባቢዎችን ጤናን ጎጂ ከሆኑ ብክለቶች በመጠበቅና ንፅሕ የመጠጥ ውኃ ለመላው ሕዝብ በማዳረስ ውኃ ወለድ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። በኤች አይ ቪ/ኤይድስ፣ በሳምባ ነቀርሳ፣ በወባ በሽታና በመሳሰሉት ተላላፊ በሽታዎች ላይ ሰፊ የመከላከል ሥራዎች ይካሄዳሉ።

4-3-3- የጤና እክስተንሽን ሠራተኞች በሽታን ለመከላከልና የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና ለመስጠት በሚያስችላቸው በቂ እውቀት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል። ለአገልግሎታቸውም ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያና የሥራ ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል።

4-3-4- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች (ካንሰር፣ ሱካር፣ የደም ግፊት ወዘተ…) በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየተስፋፉ ስለሆኑ ብቃት ያላቸውና ለተራ ዜጎችም ተደራሽ የሆኑ የሕክምና ተቋማት፣ የምርመራና የሕክምና መሣሪያዎች ወዘተ ቢያንስ በየክልሉ ከተሞች እንዲኖር ይደረጋል።

4-3-5- የግል የሕክምና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

4-3-6- ባሕላዊ መድኃኒቶችና የሕክምና ዘዴዎችም ላይ ተገቢው ጥናትና ምርምር ተደርጎ የአጠቃቀም ደረጃቸው እንዲሻሻል ይደረጋል።

### <u>4-4-ማሕበራዊ ዋስትናን በሚመለከት፡-</u>

4-4-1- የኢህአዴግ መንግሥት በችግር ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎቻችን ማሕበራዊ ዋስትናን የማስገኘት ሳይሆን ዜጎችን ያለአንዳች ዋስትና ከስራ እያፈናቀለ ችግሩ የሚባባስበትን ሁኔታ እየፈጠረ ስለሆነ በሴተኛ አዳርነትና በልመና የሚተዳደሩ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል። ስለዚህም ይህንኑ ችግር ለማስወገድ እንዲቻል ከሥራቸው የሚፈናቀሉም ሆነ ዕድሜያቸው ለጡረታ ሳይደርስ በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ የሚሰናበቱ ዜጎች ከሰጡት አገልግሎት ጋር የሚመጣጠን ክፍያ (የጡረታ አገልግሎት ካሳ) ወድያውኑ እንዲያገኙ ይደረጋል። ለጡረተኞች የሚከፈለው አበል በየወቅቱ የሚከሰተውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ባገናዘበ መልኩ ይስተካከላል።

4-4-2- በተፈጥሮም ሆነ በሌሎች አደጋዎች የአካል ጉዳተኝነት የደረሰባቸው ወገኖቻችን በአምራች ዜግነት ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል። ለኑሮአቸውም የሚያስፈልግ ድጎማም ይሰጠቸዋል።

4-4-3- አካል ጉዳተኞች ችግሮቻቸውን ያገናዘቡ የትምህርትና የሙያ ስልጠናዎች አስፈላጊው ቁሳቁስና የትምህርት መሳሪያዎች በተሟሉበት ሁኔታ እንዲያገኙ ይደረጋል። አቅማቸው በፈቀደ መጠን የሥራ ዕድል በማግኘት ከሌላው ዜጋ ጋር ልዩነት ሳይደረግ ሠርተው የሚኖሩበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል።

4-4-4- ጠዋሪ ያጡ አረጋዊያን በመንግሥትና በተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ ጊዜአቸውን የሚያሳልፉበት ማዕከላትም እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ አረጋዊያን በሕይወታቸው ዘመን ያካበቱትን ጠቃሚ ልምዶች ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፉበት ሁኔታም ይመቻቻል፡፡

4-4-5- የሀገሪቱ የወደፊት ተስፋ የሆኑት ህጻናት ሥነ-ምግባራቸውና ጤንነታቸው ተጠብቆ ያድጉ ዘንድ ልዩ ትኩረት በማድረግ በየአከባቢያቸው ተገቢው የትምህርትና የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ወላጅ አልባ ሕጻናት በእንክብካቤ ያድጉ ዘንድ አስፈላጊ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

4-4-6- የእናቶችና የቤተሰብ ምጣኔና የወልድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ፕሮግራም ተጠናክሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

4-4-7- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመከላከልና ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች ለመርዳት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር ዕርዳታን የማስተባበር ሃላፊነት ያለበት ተቋም እራሱን ችሎ እንዲቋምና ሥራውን በብቃት እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡

4-4-8- በሰብአዊ ዕርዳታ ሥራዎች የሚሠማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪክ ማሕበራት በነፃነት ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል፡፡ ከዕለት ደራሽ ዕርዳታ በተጨማሪ ተረጂውን ሕብረተሰብ ከተረጅነት እንዲላቀቅ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን እንዲያከሄዱም ተገቢው ማበረታቻና እገዛ በመንግሥት በኩል ይደረግላቸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢህአዴግ መንግስት ያወጣውና የሥራ እንቅስቃሴያቸውንና የፋይናንስ ምንጫቸውን አጣብቦ በሥራቸው ላይ መሰናክል ሆኖ የሚገኘው አዋጅ ተሰርዞ በምትኩ እንቅስቃሴያቸውን የሚያበረታታና ለሥራቸው ድጋፍ የሚሰጥ ድንጋጌ ይወጣል፡፡

### 4-5-ሴቶችንና ወጣቶችን በሚመለከት፡-

4-5-1- ሴቶች ከወንዶች እኩል ስራ የማግኘት ዕድል፣ ሀብትን የማፍራት፣ የንብረት ባለቤት የመሆንና የመውረስ መብት ይኖራቸዋል፡፡ በፆታቸው ምክንያት ምንም አይነት ልዩነት አይደረግባቸውም፡፡ የእኩልነት መብታቸውን ለማጎልበትም የትምህርትና የስልጠና እድሎችን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በእርግዝናና በወልድ ወቅትም መብታቸው ተጠብቆ በቂ እረፍት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል፡፡

4-5-2- በተለያዩ ኋላ ቀር እምነቶችና ባሕሎች ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርስባቸውን አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶችን ለማስወገድ በጥናት ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ በተለይም በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱትን ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛትን የመሳሰሉ አጓጉል ባሕሎች እንዲቀሩ የሚያደርጉ ጥብቅ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

4-5-3- ሴቶች በሁሉም የሕብረተሰብ እንቅስቃሴዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይበረታታሉ፣ የሴቶች ማሕበራትና ድርጅቶች ከገዥ ፓርቲ ጥገኝነትና ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡

4-5-4- የሀገራችን ወጣቶች በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ተንሰራፍተው የሚገኙት ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች ዋነኛ ሰለባ ስለሆኑ እየደረሰባቸው ያሉትን የሥራ አጥነትንና የኑሮ ውድነት ችግሮችን በዘላቂነት ለማስወገድ የሚያስችሉና የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ መርሐ ግብሮችና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና ሥራ ላይ በማዋል ችግሮቹ መፍትሔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

4-5-5- ወጣቶች የዜግነት መብታቸው ተከብሮ በትምህርት ውጤታቸው፣ በሙያ ብቃታቸውና በክህሎታቸው ብቻ ተወዳድረው ሥራ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠርና ሥራ ለማግኘት ተብሎ ከገዥው ፓርቲ ጋር እንዲቆራኙ እንደዚሁም መላ ወጣቶችን በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር እንዲሆኑ የሚደረግበት ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ ወጣቶች ሥራ እንዳያጡ በመስጋት በነፃነት እንዳይደራጁ የሚፈጸሚባቸው ጫናም በአስቸኳይ እንዲቀር ይደረጋል፡፡

4-5-6- ወጣቶች የተለያዩ አጉል ሱሶች ሰለባ እንዳይሆኑ ብርቱ ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚሁም መሠረት ወጣቶች በአእምሮና በአካል እንዲዳብሩ የሚያገለግሉ የመዝናኛ፣ የስፖርትና የዕውቀት ማዕከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡